በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ግንቦት 24 ቀን 2011
አዲስ አበባ

# 70ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 70ኛ መደበኛ ስብሰባ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢኮኖሚ ሪፎርም ዕርምጃዎችና ቀጣይ አቅጣጫዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

የአገሪቱን ኢኮኖሚ ለማቃናት እና ተከታታይነት ያለውን ልማት ለማረጋገጥ፣ መዋቅራዊ ኢኮኖሚ ተግዳሮቶችን በዘላቂነት ለመፍታት፣ ከመንግስት መር ኢኮኖሚ ወደ ግሉ ዘርፍ መሪነት የሚያሸጋግሩ ማሻሻያዎችን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ሪፎርሞች እድገቱን የሚያስቀጥሉ፣ የስራ አጥነትን የሚያቃልሉና የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ መሳ ለመሳ እንዲሄዱ የሚያስችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ መዋቅራዊ ችግሮችን የመፍታት ስልት እንደተጠበቀ ሆኖ የአፈጻጸም ዲስፕሊናችን ጉድለት ያመጣብንን ችግሮች ለመቅረፍ አጣዳፊና በፍጥነት ኢኮኖሚውን የሚያነቃቁ እርምጃዎች መውሰድ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢኮኖሚ ሪፎርም ዕርምጃዎችና ቀጣይ አቅጣጫዎችን የሚያሳይ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ቀርቧል ምክር ቤቱም በቀረበው ሰነድ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ በስራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

//